# ቅምሻ

ከሐዋርያ የሚያዚያ 1997 ዓ.ም (April 2007) ዕትም፤

**ከደብዳቤዎ ዓምድ ...**

**ይድረስ ለሐዋርያ አዘጋጆች፤**

ችግሩ ሁሉ ተወግዶ ውድ ጋዜጣችን ትቀጥላለች የሚል ተስፋ አለኝ:: ሐዋርያ አጉድላላች:: በተለይ በአሁኑ ጊዜ ነፃ ጋዜጦች ሁሉ ታፈነው ባለበት የሐዋርያ መውጣት በጣም አስፈላጊ ነው:: በተለይ በአሁኑ ጊዜ የለመደባቸው ትግልን ትተው ለመጪው የወያኔ ምርጫ እንዘጋጅ እያሉ ዳግም ሊያንገዳግዱና ሊያተራምሱን እየጣሩ ናቸውና በጊዜ ሐዋርያ ቸብ ቸብ ታድርግልን እላለሁ::

ደምሴ አየለ

ሀኖቨር/ጀርመን

<u>ሐዋርያ፡-</u> ውድ ደምሴ÷ በመልካም አንደበት "ሐዋርያ አጉድላለች" ማለትህ ጥሩ ማበረታቻና የድክመታችን ማደሻ ሆነን:: ብዙ ከማለት ተቆጥበን÷ "አይዞን!" እንቀጥል እንላለን:: ... ለሎቹን ደብዳቤዎች ከጋዜጣው ያንቡ፤

......................... ///// ............................

# የአቶ መለስ ቡድን በሥልጣን እንዴት እስካሁን ለመቆየት ቻለ? ለመለወጥስ መፍትሄው ምንድን ነው?

*ዶ/ር ወርቁ አበበ*

እንደሚታወቀው ሁሉ በግንቦቱ 7÷ 1997 ዓም ብሄራዊ ምርጭእ የአቶ መለስ መንግሥት በኢትዮጵያ ሕዝብ በማያሻማ ሁኔታ ተተፍቷል:: ሆኖም ይህ የሕዝብምርጫ በዚህ መንግሥት ተቀባይነት አላገኘም:: በጊዜው የነበረውን ሁኔታ ከግንዛቤ በማስገባት÷ የምርጫው አሸናፊ በሆኑት ተቃዋሚ ድርጅቶች ስምንት አማራጭ የመደራደሪያ ነጥቦች ቀርበው ጉዳዩ በሌላ መንገድ በሰላም እንዲያልቅ ተሞክሮ ነበር:: የአቶ መለስ መንግሥት ግን እንደገና ይህንንም አልቀበልም በማለት ቀደም ከፈጸመው ስህተት ትምህርት ወስዶ አምባገነንነቱን ሊደባብሰው ችሏል:: በዚህ ሁኔታ ቀድሞበያዘው ሥልጣን በህገወጥነት እስካሁን ለመቆየት በቅቷል::

ለመሆኑ ምን አይነት ዘዴዎችን እየተጠቀመ ነውይህ ህገ-ወጥ መንግሥት እስካሁን በስልጣን ሊቆይ የቻለቻው? ለሚጠቀምባቸው ዘዴዎች የመቋቋሚያ ወይም የማፍረሻ መንገዶች አሉ? በሥልጣን ለመቆየት ይህ መንግሥት ከሚያደርጋቸው ጥረቶች በተጨማሪ ተቃዋሚዎች ይህንን ላለምቋቋም ወይም በቀላሉ ለማራመድ ምን አይነት ድክመት ያሳያሉ? የሚጠበቅባቸውን ግዴታ እየተወጡ ነው? ከላይ እንደተጠቆመው ለነዚህ ጥያቄዎች መልስ ለማግኜት መሞከሩ ሕዝቡ ለሚያካሄደው ትግል ጠቃሚ ሊሆን ይችላል::

1) የአቶ መለስ ቡድን የሚያደርገው፤

ቀጥሎ የተመለከቱት በሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት በዚሁ ለመቆየት ብሎ የሚጠቀምባቸው ዋነኛዘዴዎች ናቸው ብዬ እገምታለሁ::

1ኛ) ሕዝብን መከፋፈል፡- ብሶት ያለበት ሕዝብ አንድላይ በመሆን መንግሥት የሚያደርስበትን በደክ እንዳይከላከል ወይም እንዳያከሽፍ ለማድረግ በተለያዩ መንገዶች በመነጣጠል ያዳክማል:: በዚህ መሠረት የከፋፍሎ መግዛትን የአስተዳደር መመሪያ ያካሂዳል:: ከሚከፋፍልባቸው መንገዶች መካከል የሚከተሉት ጎልተው የሚታዩ ናቸው:: .......... ሙሉውን መልእክት ሐዋርያን አግኝተው ያንቡ፤

................................//////.........................................

# ቅሌትና እውነት

*ሻለቃ ግርማ ይልማ ቡልቡላ*

የተከበራችሁ አንባቢዎቻችን ብዙዎቻችሁ በጉጉት ትጠብቁት የነበረው ይህ ተከታታይ ዘገባ ከሚገባው በላይ ጊዜ ወስዶ በአዝጋሚነት በመከተሉ ይቅርታ እየጠየቅን፥ የታሪኩን ተከታታይነት ለመጨበጥ ያለፈውን እትም ማገናዘብ ማስፈለጉን ማስታወስ እንሻለን። በመጠኑ የት ላይ እንደነበርን ለማስታወስ ያህል፥ ጸሃፊው በደርግ ሥርዓት ባለሥልጣን ከነበረና ዛሬም ባለሥልጣን ሆኖ ከሚገማሸር ድንገተኛ ትውውቃቸው ጋር ጀምረውልን የተቋረጠው ታሪክ እንዲህ ነበር ቀጥሎ የነበረው፡-

*እኔ በጣም ግልጽ ሰው ነኝ። የምናገረው እንደመጣልኝ ነው። ጥያቄህና መልስህ አሳዝ ኖል።" አሉኝ። ንግግራቸውን ሲጨርሱ "ለመሆኑ እኔን በቅርብ ያውቁኛል?" ስል ጠየቅሁዋቸው። "አላውቅህም። የደርግ አባል አይደለህም እንዴ?" ሲሉ ጠየቁኝ። "የደርግ ማስታወቂያ ኮሚቴ አባል ነበርኩ" አልኳቸው። መሳሳታቸውን እየተረዱ ሲመጡ ተከላካይ መሆን ጀመሩ። "ቢሆንም ልዩነት የለውም ተጠያቂ ነህ" በማለት ደመደሙ። ዘለግ ላለ ጊዜ በክፍሉ ውስጥ ፀትታ ነገሰ። እኔም ለሰላምታ የተዘረጋ እጄን ሰብስቤ ተቀምጥሁ። እንግዳው ለመሄድ ከመቀመጫቸው ሲነሱ እኔም ከመቀመጫዬ ብድግ በማለት "እንተዋወቅ" በማለት እጄን እንደገና ዘረጋሁ። "በላይ ነጋ እባላለሁ" አሉኝ እጄን እየጨበጡ። "የበለጠ ብንተዋወቅ ይሻላል" አልኳቸው። "ትዝትብኛለህ!" አሉ እንደገና በቁጣ። "እረ! ዛ ቻ አይደለም" አልኩ የበላይ ነጋ ባህርይ ግራ ገብቶኝ። አሁንም እኔ ግልጽ ነኝ። ውስጥ ውስጡን አልሄድም። ጌታቸው ገዳሙ፥ ወንዳየ ን ምህረቱና ተስፋዬ ወልደ ሥላሴ በቅርቡ ይፈታሉ።*

*"በላይ ነጋ የሚለውን ስም ከዚህ በፊት የሰማሁ ይመስለኛል"*

*"በደርግ ዘመን ስታሥሩኝ ነበር ስሜን የሰማኸው?*

*"እኔ ሰዎች እንዲታሠሩ የሚያደርግ የሥራ ድርሻ አልነበረኝም። እንኳን ንጹህ ሰው ተጠርጣሪ እንኳን ሲታሠር ያሳዝነኛል። ለመሆኑ በደርግ ዘመን ጋዜጣ ያነቡ ፥ ሬዲዮ ያዳምጡና ቴሌቪዥን ይመለከቱ ነበር?"* የሚል ነበር። ቀጣዩ እነሆ፥፤ መልካም ቆይታ።

"ሡርቶ አደር ጋዜጣና መስከረም መጽሄት እንኳን አይቀሩኝም ነበር። ለስምንት ዓመታት በታሰርኩበት ጊዜ ብቻ ከምንባብናከግልጽ መረጃ ተለይቼ ነበር። እድሜ ለእናንት!" በማለት ከጥብቅናው ጽ/ቤት ወጥተው ሄዱ። ከእንግዳው በሰላም ከተለያየ በሁዋላ ኮሎኔል በላይ ነጋ የህይወት አንጋፋ መሪ የአቦይ ስብሃት ነጋ ውንድም መሆናቸውን ተረዳሁ።

2. የግል ማስታወሻ ቁጥር 185

ሰኔ 7 ቀን አቶ ገዛኸኝ ገብሬን አዲስ አበባ ዘውዲቱ ሆስፒታል አጠገብ አገኘሁት፡ ገዛኸኝ ገብሬ በእውነት ለሕዝብን ሮለሀገር አላማ የቆመና በሕዝባዊው ንቅናቄ ውስጥ የሚናገረውንና የሚጽፈውንበተግባር ሆኖ የተገኘን ሮክቅለትና ከሥልጣን ብልግና ነጻ መሆኑን ስለማውቅ በመገናኘታችን በጣም ደስ አለኝ። ፍልውሃ አካባቢ ወደሚገኘው መዝናኛ ጎራ ብለን ስለወቅቱ የሀገራችንና የሕዝባችን ጉዳይ በሰፊው ተወያየን። በውይይታችን መካከልከአንድ ወር በፊት ከእሥር መፈታቱንና በቁጥጥር ውስጥ በነበረበት ወቅት የተገነዘበውን አስረዳኝ።

በሐምሌ ወር 1983 ዓ.ም ከምጽዋ ወደ ኢትዮጵያ በድፍረት በመመለስ ሰንዳፋ በእሥር በነበሩ ከፍተኛ የደርግ ባለሥልጣኖች መካከል የሞቀ የውይይት ርእስ እንደነበርኩ ግልጽ አደረገልኝ። በዚያ ቀውጢ ጊዜ ባለሥልጣን ራሱ ከአገር ለመውጣት ልዩ ጥረት ሲያደርግ ግርማ ይልም ሮለምን መጣ? የሚሉ ጥያቄዎች እየተነሱ ሦስት አማራጭ ምክንያቶች ይደረደሩ እንደነበር ነገረኝ።

2.1. አስቀድሞ ከኢህአዴግ ጋር ሚስጥራዊ ግንኙነት ስለነበረው ምንም እንደማይደርስበት ማረጋገጫ ስላገኘ ነው፤

2.2. ጥንቃቄና ማስተዋል በጎደለው ጀብደኝነትና አጉል ድፍረት ስለሆነ በቅርቡ ከእኛ ጋር ይሆናል፤

2.3. እኛ የምናውቀው ግርማ ይልማ በግሉ በሕዝብና በሀገር ላይ የፈጸመው በደል ስለሌለና በንጽህናውም ስለሚተማመን በጋራ ሃላፊነት ሊደርስበት የሚችለውን እስርም ሆነ ሌላ ስቃይ በጸጋ ለመቀበል ቆርጦ የመጣ ነው። ይህ የመጨረሻው ግምታዊ አስተያየት የእርሱና የጥቂት የደርግ ባለሥልጣኖች አቋም እንደነበር ግልጽ አደረገልኝ።

የግል ማስታወሻ ቁጥር 263፤

ታህሳሥ 19 ቀን 1986 ዓ.ም አራት ኪሎ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት አጠገብ አንድ ወጣት በድንገት ታክሲ ጋቢና ውስጥ ተቀምጨ አይቶኝ ታክሲውን አስቁሞ ዘሎ ገባ። ፒያሳ ብሪቲሽ ካውንስል ቤተ መጽሃፍ አጠገብ ከታክሲው ስወርድ ተከትሎኝ ወረደ። ሊያናግረኝ እንደፈለገ ስለገባኝ ሰላም አልኩት። እርሱም "ቴዎድሮስ እባላለሁ፤ የበረሃ ስሜ ነው። አንተ አታውቀኝም እኔ ማንነትህን በሚገባ ተከታትያለሁ። ደርግ ፅ/ቤት ከሻምበል ጌታቸው አግዴናከሌሎቹም ጋር በቅርብ ሥሰራ ነበር። በሩቅ ታክሲ ውስጥ ሳይህ ዐይኖቼን ማመን ተሳነኝ። ይህ ሰው ካላበደ በስተቀር ሰው ሁሉ በደርግ ኢሠፓነትና በንክኪነት ወንጀልበገፍ በሚታሠርበትና ቁምስቅሉን በሚያይበት ጊዜ እራሱን ለሥቃይና ለመከራ ለመዳረግ እንዴት ይመጣል? የሚል ጥያቄ በቅጽበት አእምሮዬ ውስጥ ስላቃጨለ ሳታመልጠኝ ዘልዬ ታክሲ ውስጥ ገባሁ" አለኝ። እዚያው መንገድ ላይ ቆመን ስለወቅቱ የኢትዮጵያ ሁኔታ በሰፊው ተወያየን። በሕዝቧና በኢትዮጵያ የደረሰው ከፍተኛ አደጋ በማንም ያልተጠበቀና ያልተገመተ ዱብ እዳ እንደነበር ተስማማን።

"እኔ ምንጊዜም ከአገሬ ከኢትዮጵያ አልወጣም። ሕዝብ የማስተባበርና የማንቃት ተግባሬን በህቡእ እቀጥላለሁ" በማለት አቋሙን በልበሙሉነት ገለጸልኝ። እኔም በአገር ውስጥ ቆይቶ የመታገል አቋሙን በአድናቆት ደግፌ ስደት የሚወደድ አማራጭ እንዳልሆነና እኔም በዚያ አስቸጋሪ ወቅት ወደ አገሬ የተመለስኩት እዚያው ሆኜ አቅሜ የሚፈቅደውንለማከናወን እንደነበር ገለጽኩለት። "ጓድ ግርማ፥ የአንተ አቋምና ድርጊት የሚገርም ነው። በሥልጣን ላይ ሆነህም "ክሊኪሽ" (ወገንተኛ) አልነበርክም። ፍትሃዊና ትክክል የመሰለህን በመርህ ላይ ተመስርተህ አከናውነሃል። ወያኔዎች ከእኛም ውስጥ ወኪሎች ነበራቸው። ለያንዳንዳችን በቂና ዝርዝር መረጃ አላቸው። ወደ

ኢትዮጵያ እንደተመለስህ ወዲያው ያላሠሩህ አዝነውልህ እንዳይመስልህ፡፡ ጀብደኞች ስለሆኑ ደፍረህ ወደ አገርህ በመመለስህ አድንቀውህ ሊሆን ይችልላ፡፡ አትዘናጋ፤ ተጠንቀቅ፡፡ ዛሬ የኢትዮጵያ ፖለቲካ አቅጣጫ የሌለውና የተሳከረ ስለሆነ ምንም ውስጥ አትግባ፡፡ እኔም ወደሰሜን ኢትዮጵያ በቅርቡ እመለሳለሁ፡፡" ብሎ ተሰናበተኝ፡፡

የተከበሩ የመቶ አለቃ ጳውሎስ፥ በእርግጠኛነት የተመኙልኝ የወህኒ ቤት ህይወት በሚመለከት ብዙ ገጠመኞች ቢኖሩኝም ለጊዜው እነዚሁ ይበቃሉ፡፡

ስለደርግ መዋቅርና አሰራር አለማወቅ፥ ወይም እኔን በጣም አስከፊና ጭካኔ የተሞላበት የንጉሠ ነገሥት ሃይለ ሥላሴ ከፍተኛ ባለስልጣናታን ጥቂት ተቃዋሚዎች የጀምላ የደቦ ግድያ ጋር ለማቆራኘት የተከበሩ የመ/አልቃ ጳውሎስ ስለገለጡት ውሸትና ቅጥፈት የእኔን እውነት በሃቅ አቀርባለሁ፡፡

"ህዳር 14 ቀን 1967 ዓ.ም ደርግ የኸርንጀሮ ተስካር በመሰል ስብሰባ ስድሳ ሰዎች ላይ የሞት ፍርድ በፈረደበት ዕለት የስብሰባው ቃለ ጉባኤ ያኸርዎች ሻለቃ ፍስሃ ገዳ፥ የእሥር አለቃ ግስጽ ተጫኔና እርስዎ ነበራችሁ" ብለዋል መ/አለቃ ጳውሎስ፡፡ ... ይህን ሰፊ የመልስ ምት ሐዋርያን አግኝተው ያንቡ፤

............................///////.......................................................

# ሥነ-ግጥም

## ብቻ ተሞሽሩ

*ከዶ/ር ፈቃደ አዘዘ*

ላንቺ ብሎ ነበር
በቁም ለተገነዝሽ፥
አፍሽን ለተለጎምሽ፥
ለዲዳ እናቱ፥
ሰው አፈርን በልቶ ሰው አፈር መግባቱ፤
ላንቺ ብሎ ነበር ለበድን እናቱ፡፡

አንቺን መሳይ ግዑዝ በእናቱ መስሎ፥
የምጥ መከራዋን፥
ማሳደግ እዳዋን፥
መላውን የእሷ እዳ ያንቺ እዳ አድርጎ፥
እዳዋን ለመክፈል ያንቺን እዳ ከፍሎ፥
ነበር ሰው መሞተ፥
እዳውን ሊወጣ በስቃይ በሞቱ፡፡

ነግሮሽ ባትሰሚ
ጠይቆሽ ዝም ብትይ፥
ዐይኑ ተንቆርዝዞ፥
እንባ ደም አርግዞ፥
ባትጨነቂለት፥
ምን ተዳዬ ብሎ እድሜውን ማነቁ፥
ላንቺ ብሎ ነበር ለበድን እናቱ፥
የልጅሽ ህልፈቱ፡፡

ባልተሟሸ ድስትሽ ወጥ እንድታፈይ፥
ባልታጠነ ጋንሽ ጠጅ እንድትጥይ፥
ድር ባደራ እንዝርትሽ ኩታ እንድትፈትይ፥
ነበር የሞተልሽ፤
የሱን ህይወት ጋርዶ ያንቺን ሊገልጥልሽ፡፡

የዘበት ሳቅሽን ከንቱ ግልፈጣሽን፥
የይምሰል ዘፈንሽን አይረባ መዝሙርሽን፥
ገፍፎ ከላይሽ ላይ፥
እሰዬሽን እንጂ ወይኔሽን እንዳያይ፥
ነበር ያለፈልሽ፥
ዓለሙን ጨፍልቆ ዓለምሽን ሊሰጥሽ፡፡

ጡትሽን ሳይጠባው ሲነጥፍ በማየቱ፥
ገንፍሎ ቢወጣ የኑሮሽ ምሬቱ፤
ወዝሽ ተንጠፍጥፎ ስትደርቂ አይቶ፥
ምስኪንነትሽን ከእናቱ አስተያይቶ፥
ልቡን ቢፈነቅል ወኔውን ቢያከረው፥
ነው ልጅሽ ያለፈው፥
የመከራ እድፍሽን በሞቱ ሊጠርገው፡፡

ፋጭ ያወጣ አካልሽ ጨርሶ የወረዛ፥
ለህቱ እንዲያምር እምቡጡ እንዲበዛ፥
ነው እሱን የሸጠ ላንቺ ህይወት ሊገዛ፡፡

ከል ብትለብሽበት ብትከናነቢ፥
ውበትሽ ተገፎ ጥላሸት ብትለብሽ፥
በእናቱ አንቺን አይቶ ሊሆንልሽ ዋቢ፥
ነበር የሞተልሽ ኖረሽ እንድትዋቢ፡፡
ያ ሕያው ሰውነት ዛሬ የበደነ፥
የእናቱ ሰቆቃው በአንቺ ያልታጠበ፥
ጊዜውን ጠብቆ በቀናት ቀጠሮ፥
የቁም ሙት ትንሣኤሽ ከሱው ጋር ተጣምሮ፥
መዝፈኛሽ ቀን ሲደርስ ሙሾሽ ተገንዞ፥
ካጠገብሽ ቁሞ ካንቺ ተጠግቶ፥
ቂሙን ሁሉ እረስቶ፥
ከበሮ ይደልቃል፥
ጭብጨባ ያቀልጣል፥
እስክስታ ይወርዳል፡፡

ለዋይታው ደንቁረሽ፥
በሞቱ ባታለቅሽ፥

ዐይንሽን ባታሽም ይሉኝታ ብለሽ፥
ከቂም አይቆጥረውም ከልቡ መዝግቦ፥
የዝምታሽ ምንጩን ያውቃል አበጥሮ፥
ከጥንት ጀምሮ፥
ዘመን ሁሉ ሲያልፍ ዘመን ተሸሮ፥
ስምና መንፈስሽ ተረግጦ ተወግሮ፥
የስሜት ህዋስሽ ላይደን በድኖ፥
ስሜት አልባ ያረገሽ ስሜትሽን አባክኖ፥
ያንዱ ልጅሽ ህልፈት በሌላው ተጻምሮ፥
እንደሆነ ያውቃል።

ዛሬም የሱ ህልፈት፥
ለስቃይ ባህርሽ አንድ ሌላ ጠብታ፥
ለደነዘ አካልሽ ኢምንት ጠቅታ፥
ለደደረ አንጎልሽ አይረሳ ውልፍታ፥
እንደሆነ ያውቃል።

ስለዚህም ልጅሽ፥
አያሳፍርሽም - በደስታ ተነሽ፥
አይቀነስብሽም - የሙሽራ ወግሽ።

አንቺ ተሞሽሪ እንጂ
ከበሮ ይደለቃል
ጭብጨባ ይቀልጣል
እስክስታ ይወርዳል።

(ለግንቦት 1965 ዓ.ም የ/ሮ ስህን ት/ቤ ተማሪ - ሰማእታት)
........ ሌሎቹን ግጥሞች ሐዋርያ ላይ ያንቡ

................................./////.................................................................................

# መብት በትግል እንጅ በልመና አይከበርም!

**ያሌሊ ኒባምሊ**

ይህቺን አጭር ማስታዎሻ የጻፍኩት የአፋር ሕዝብ በኢትዮጵያዊነቱ ጸንቶ የራሱን ባህል፥ ቋንቋና ሃይማኖት ጥብቆ ሊኖርበት የሚችለውን የራስ ገዝ ጥያቄውን ለመመለስ የሚያቅማሙ የኢትዮጵያ መንግሥትና የፖለቲካ ድርጅቶች በአንድ በኩል፥ የአፋር ምድር ከባብኤል መንደብ ፊት ለፊት የሚገኘውን የቀኝ ባህር ስትራቴጂክ ጠረፎችን ከምጽዋ እስከ ዘይላ በማዋሰኑ በክልሉ የባህር ጠረፎች በጂኦፖለቲካ ጠቀሜታነቱ ምክንያት በብሄረሰቡ ላይ የሚደርሰው የሃያላን መንግስታት ተጽእኖ በሌላ በኩል ሆኖ የብሄረሰቡ የመኖር ህልውና ሳይቀር በጥያቄ ምልክት ውስጥ በሚገኝበት በአባቶቻችን ከፍተኛ ጥረት የተገነባው የአፋር አንድነት ከምንጊዜውም ጊዜ በከፋ ሁኔታ አደጋ ላይ የወደቀበት ወቅት ነው።

በተጨማሪ የዛሬ 30 ዓመት ገደማ በመጀመሪያ ከ2ኛው ዓለም ጦርነት ፍጻሜ ቀደም ብሎ በሱልጣን ማሃመድ ያዮ የተነሳውን የአፋር አንድነት ጥያቄ በማንገብ የትግላችን ግብ በብሄረሰቦች እኩልነት ላይ በተመሠረተች ታላቋ ኢትዮጵያ ውስጥ የአፋኗን ራስ ገዝ (አውቶኖሚ) እውን ማድረግ ነው ብሎ ለሕዝቡ ቃል የገቡትን ዓላማ ስተው አውቀውም ሆነ ሳያውቁ ሕዝቡን ከባህሉ ውጭ መፍትሄ የሌለው የፖለተካ ውዝግብ ውስጥ እያስገቡት፥ እንዲያውም ይባስ ብለው በአውሳ ሱልጣናት መሪነት ከጎሳ ፖለቲካ ወደማእከላዊ የሱልጣናት አስተዳደር ከ1672 ጀምሮ የተሸጋገረውን ሕዝብ በጎሳ ሀራጎች ለመሸንሸን ያለምንም ይሉኝታ በሰፊው በሚንቀሳቀሱበት የአፋር ሕዝብና አገሩ ለከፍተኛ አደጋ በተጋለጠበት ወቅት ነው። ... በሐዋርያ ላይ ቀሪውን ያንቡ

.................... /////// .................................

# ካዜናው ባሻገር

**መስፍን ታምራት ፤ናይሮቢ**

ሀባሪ ፤ ጃምቦ።

"ሞጃ ፓ ሞጃ" እንዲሉ ኬንያውያን፥ ወደፊት በቀጥታ ስንጓዝ/የካርቱም ጓደኞቻችን "ኤምሺ ጠዋሊ" እንዲሉ፥ ነገ ቀና ሆኖ ውድ ሐዋርያችን ከችግር ተላቃ፤ የድብቅም የይፋም ጠላቶቿን አሳፍራ በተከታታይ እንድትወጣ እየተመኘሁ፥ ይችን ተለምዳ የነበረች አምዴን ልጀምር።

የሀገራችን ጉዳይ መቸም ሴትየዋ "ከክፉ ተወልጄ ስፈጭ አደርኩ" እንዳሉት ሆኖብን ችግራችን ቀነሰ ስንለው እየጨመረ ፣ እያደር አልፈታ አልጠፋ ባይነቱ እየከረረ፣ እየተዋለደ መሄዱደግሞ ለቀቢፀ ተስፋ ባይዳርገንም እያበሳጨን ያለ ክስተት ሆኗል፡፡ ያ ግሎና ፈንድቶ ዓለምን ያስደነገጠ ህዝባዊ ትግል፣ ጥራዝ ነጠቆቹም በተለመደው ችኮላ ቃሉ በአማርኛ ሆነ አሮሚፋ ትርጉም ባይኖረውም "ሱናሚ" ብለውት የነበረው ትግል ከደረሰበት ማዕበላዊ ጫፍ ወርዶ መባጀት ያቃተው ወንዝ ዓይነት ሆኖ ሲገኝ መቸም ሁሉም ዜጋ ምነዋ ማለቱ የሚጠበቅ ነው፡፡ ጃል ምን አደጋ ደረሰብን፣ ምን ሆንን ማለቱ ሲያንስ ነው፡፡ ዛሬ ጣት ጥቆማውን ቀነስ አድርገን መሰረታዊ ችግሮችን በተመለከተ ትኩረት ሰጥተን እንመርምር ስንል ደግሞ ድርጅቶች በፈፀሚቸው ትንሽም ትልቅም ስህተቶች የተነሳ መለስ ዜናዊ ጊዜ መግዛቱ ግልፅ ነው፡፡ አበቃለት ላይ ደርሶ መለስ ብሏል፣ ዳግም የበላይነት ሊይዝም እየተፈጨረጨረ ነው፡፡ ነገሩ ላለፈ ክረምት መጠለያ አይሰሩ ነውና ዛሬ ምን ይደረግ ምን ይጠበስ ለሚለው በጋራ መልስ መስጠቱ ቀዳሚ መሆን ያለበት ጉዳይ ነው፡፡

ዛሬ ያለንበት ሁኔታ ምን ይመስላል? .... ይህን ወቅታዊ አቅርቦት በዚህ ወሩ የሚያዚያ የሐዋርያ እትም ላይ እንዲከታስሉ እንጋብዝዎታለን፡፡

...................................... ///..................................

ሐዋርያ ብዙ መሰናክሎችን ተቋቁማ የቀጠለች መሆኑን እያበሠርን፥ ደህረ-ገጻችንም (www.hawarya.net) የተቀላጠፈ አገልግሎቱን ጀምሯል፡፡ ዕለታዊና ወቅታዊ ዜናዎችን በደህረ-ገጻችን ላይ እንዲከታተሉም በዚህ አጋጣሚ እናሳስባለን፡፡

ሐዋርያን ለማዘዝ የምትሹ ሁሉ ክፍያችሁን በሚከተለው እድራሻ ብትልኩል በደስታ ተቀብለን አገልግሎታችን እንቀጥላለን፦

Hawarya
1116 Wilson Ave.
P.O.Box 66036
Toronto, Ontario (Canada)
M3M 1G7

Tel/Fax (905) 799-2193